በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትራንስፖርት ቢሮ

ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
TRANSPORT BUREAU

## መመሪያ ቁጥር 155/2016

# የአዲስ አበባ ከተማ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በከተማው የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሞተር ብስክሌቶች በከተማው ነዋሪና የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጥሩትን አላስፈላጊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሞተር ብስክሌት ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ 04/2011 ተግባራዊ ሲደረግ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በአገልግሎቱ መቋረጥ ምክንያት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር መዳረጋቸውን በጊዜ ሂደት በመረዳት የቁጥጥር ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ አገልግሎቱ ህጋዊ አደረጃጀትና ፍቃድ ኖሮት ማስቀጠል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚሁ መሰረት ማሻሻያ የትግበራ ጥናት ግኝቶች ማረጋገጥ በመቻሉ፤ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክልን በተመለከተ የተካተቱ ድንጋጌዎች በመኖራቸው እና ከሁለት አመት በኋላ ማንኛውም ሞተር ሳይክል ወደ ኤሌክትሪክ እንደሚቀየርና አዲስ ፈቃድ ለኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክ ብቻ እንደሚሰጥ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1 **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 155/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2 **ትርጉም**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
3. **"ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ነው፣
4. **"የኦፕሬሽን ዘርፍ"** ማለት በቢሮው ውስጥ የሚገኝ የህዝብና ጭነት ትራንስፖርት የአደረጃጀት፣ ስምሪትና ክትትል እንዲሁም፣ የስምሪት ቁጥጥር ሥራን በበላይነት የሚመራ የሥራ ክፍል ነው፤
5. **"ኦፕሬተር"** ማለት የንግድ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ወይም ድርጅት ነው፤
6. **"የብቃት ማረጋገጫ"** ማለት በቢሮው በሞተር ሳይክል ወይም በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ማኀበራትና ድርጅቶች የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤
7. **"ተጠቃሚ"** ማለት የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል መከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ ወይም ጂፒኤስ በመግጠምና ፈቃድ በመውሰድ በግለሰብ፣ በድርጅትና በማህበር ስም በተመዘገቡ ሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አማካኝነት በከተማው ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚቀርብ ግለሰብ ወይም ኦፕሬተር ነው፤
8. **"ዩኒፎርም"** ማለት የአንድን ተቋም ወይም ድርጅት ሞተር ሳይክል ወይም የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ በተለየ መልኩ የሚገልጽ የተለየ የሥራ ልብስ ነው፤
9. **"ሞተር ሳይክል"** ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ባለሁለት ጎማ ባለሞተር የነዳጅ ሃይል ተጠቃሚ ተሽከርካሪ ነው፤

10. **“የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል”** ማለት ክበደቱ ከ250 ኪሎ ግራም ያልበለጠ ባለሁለት ጎማ የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
11. **“የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል መከታተያ ሥርዓት”** ማለት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሁለቱንም ሞተር ሳይክል ወይም የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል መረጃ በማስተላለፍ የሞተር ሳይክሉን እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው፤
12. **“የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል መቆጣጠሪያ ሥርዓት”** ማለት የጂፒኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአንድን ሞተር ሳይክል ወይም የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ከፍጥነት ወሰን በላይ ሲያሽከረክር የቀይ መብራት ምልክት እንዲሰጥ በማድረግ የሞተር ሳይክሉን እንቅስቃሴ መቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው፤
13. **"ተቆጣጣሪ"** ማለት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችንና የትራንስፖርት ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን ወይም አግባብነት ባለው አካል የተመደበ ወይም የፖሊስ አባል ነው፤
14. **"ማህበር"** ማለት የኦኘሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ባለንብረቶች ወይም ኦኘሬተሮች የሚያቋቁሙት ማኅበር ወይም ድርጅት ነው፤
15. **“የማህበር ፈቃድ"** ማለት ማህበራትን ለማደራጀት ስልጣን ባለው አካል የተመዘገቡ በማኅበር ተደራጅተው የንግድ የሞተር ሳይክል ወይም በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለወሰዱ ባለንብረቶች የሚሰጥ የማኅበር አደረጃጀት ፈቃድ ነው፤
16. **"የድርጅት ፈቃድ”** ማለት ከፈቃድ ሰጭ አካል በሞተር ሳይክል ወይም በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ትራንስፖርት የመልዕክት አገልግሎት ስራ ዘርፍ ለመሰማራት እንዲቻል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
17. **"የትራንስፖርት አገልግሎት”** ማለት በሞተር ሳይክል ወይም በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አማካኝነት የሚሰጥ ዕቃዎችን የማጓጓዝ አገልግሎት ነው፤

18. **"የፍጥነት ወሰን"** ማለት በዚህ መመሪያ የተደነገጉ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ የሚገድብ የማሽከርከር ፍጥነት ጣሪያ ነው፤
19. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
20. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ያገለግላል፡፡

## 3 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የሞተር እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነትና አደረጃጀት

## 4 የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት

የትራንስፖርት አገልግሎት አይነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

1. በተገጠመ የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ የተለያዩ እቃዎችንና መልእክቶችን በክፍያ ማመላለስ፤
2. ለግል የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጎት መጠቀም፤

## 5 የትራንስፖርት አገልግሎት ፈቃድ ስለማግኘት

1. በአዲስ አበባ ከተማ ተመዝግቦ አገልግሎት ለመስጠት አዲስ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ለኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አገልግሎት ብቻ ነው፡፡ ይህ መመሪያ ከወጣ በኋላ የሞተር ሳይክል አዲስ የአገልግሎት ፈቃድ አይሰጥም፡፡
2. በከተማው ውስጥ ምዝገባ በማካሄድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሞተር ሳይክሎች እና በማህበር የተደራጁ የሞተር ሳይክል ባለንብረቶች በሞተር ሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰማሩ ቢሮው ፈቃድ ይሰጣቸዋል፤
3. በማህበር በመደራጀት በሞተር ሳይክል ትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት ፈቃድ የሚሰጠው በአዲስ አበባ ከተማ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን በኮድ 3 የተመዝበ መሆን ይኖርበታል፤

4. በአዲስ አበባ ከተማ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን በኮድ 2፣ በኮድ 3 እና በኮድ 4 ተመዝግቦ የሚገኝ ሞተር ሳይክል ወደ ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል መለወጥ ከፈለገ አስፈላጊውን መስፈርት ካሟላ ቢሮው በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፤

5. በአንቀፅ አምስት ንዑስ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በስራ ላይ የሚገኙ የሞተር ሳይክሎች ወደ ኤሌክትሪክ መለወጥ ከፈለጉ፤ በእጃቸው ላይ ያለውን የሞተር ሳይክል ስለማስወገዳቸው ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

6. በአዲስ አበባ ከተማ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን ያልተመዘገበ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል በከተማው ውስጥ በትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት ፈቃድ አይሰጠውም፤

7. ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከውጪ ሀገር ስደት ተመላሽ የሆኑ የከተማ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የአገልግሎት ፈቃድ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ እና ወደ ሥራ ከሚያሰማራቸው ከሚያቋቁማቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅት ደብዳቤ ሲያቀርቡ 1 (አንድ) የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ ይፈቀድላቸዋል፤

8. የመንግስት መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች፣ ባለኮከብ ሆቴሎች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የላብራቶሪ ድርጅቶች፣ ፋርማሲዎችና በመድሃኒት ማምረትና ማመላለስ ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች እና የግል ሆስፒታሎች ከየመስሪያ ቤታቸው ህጋዊ ደብዳቤ ሲያቀርቡ የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ፈቃድ ይሰጣቸዋል፤ ቢሮው ከነዚህ ከተጠቀሱት ድርጅቶች በተጨማሪ ሌሎች ጥያቄ ሲያቀርቡና አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው ሊፈቅድ ይችላል፤

9. በከተማው ውስጥ ለግል ትራንስፖርት አገልግሎት ለማዋል በኮድ 2 የተመዘገቡ ሞተር ሳይክሎች በስሙ ለተመዘገበ ግለሰብ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፈቃድ ይሰጠዋል፤

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (6) እና (7) ከተገለፁት ውጭ በከተማው አዲስ የሞተር ሳይክል ምዝገባ ወይም ከሌሎች ክልሎች በዝውውር በማስተላለፍ በኮድ 3 ሆነ በኮድ 2 ለማንቀሳቀስ ፈቃድ አይሰጣቸውም፤

11. በስራ ላይ የሚገኙ የሞተር ሳይክሎች በቀጣይ 2 ዓመት ወደ ኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል መለወጥ ይጠበቅባቸዋል፤ ለዚህ አፈፃፀም የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት በቢሮው የሚዘረጋ ይሆናል፤

12. በአዲስ የዴሊቨሪ፣ ዕቃዎችን የማመላለስ ሥራ ዘረፍ መመዝገብ የሚፈልጉ በማህበር የተደራጁ እና የሚሰጣቸው ኮድ 3 ሰሌዳ ሆኖ ዝቅተኛው የአባላት ቁጥርም 250 (ሁለት መቶ ሃምሳ) እና ከዚያ በላይ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 6 ፈቃድ ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

1. በተሽከርካሪው ላይ የመከታተያና መቆጣጠሪያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ አስገጥሞ የሚቀርብና ባለስልጣኑ ፍቃድ ከሰጣቸው የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል የመፈጸም፤
2. በአንቀፅ አምሰት 5 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ለመስጠት፡-
   - ሀ) በቢሮው እውቅና ያለው ማህበር አባል መሆን፤
   - ለ) በቢሮው የጸደቀውን የማህበሩን አርማ ወይም ምልክት በሞተር ሳይክሎቹም ሆነ በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ላይ ማስተካከል፤
   - ሐ) ለመልዕክት አገልግሎት የሚሰማራ ሞተር ሳይክል ሆነ የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል ቢጫና ሰማያዊ 6 ሳ.ሜ በ 6 ሳ.ሜ ዳማ ቀለም የሞተር ሳይክሉ አካል መቀባት፣
   - መ) በቢሮው የተመረጠውን የአሽከርካሪ ዩኒፎርም እና መለያ መታወቂያ ማዘጋጀት፤
   - ሠ) ለመልዕክት ማመላለስ የሚሰራ ከሆነ በቢጫና ሰማያዊ 6ሳ.ሜ በ 6ሳ.ሜ ዳማ ቀለም ዩኒፎርም ማዘጋጀት፣
   - ረ) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (6) እና (7) የተገለጹት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በሚመለከተው አካል ዕውቅና የተሰጣቸውን አርማ ወይም ምልክት በሞተር ሳይክል እንዲሁም በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ላይ

በመለጠፍ እንዲሁም ተቋሙን የሚገልጽ የአሽከርካሪ ዩኒፎርም፣ ሎጎ እና መለያ መታወቂያ ማዘጋጀት፤

ሰ) የግል ሞተር ተንቀሳቃሽ ከሆነ ሙሉ ውሃ ሰማያዊ ቀለም ዩኒፎርም ማዘጋጀት፣

ሸ) የድርጅት ሞተር ተንቀሳቃሽ ከሆነ ሙሉ ብርቱኳናማ ቀለም ዩኒፎርም ማዘጋጀት፣

ቀ) የመንግስታዊ ተቋማት ሞተር ተንቀሳቃሽ ከሆነ ሙሉ አረንጓዴ ቀለም ዩኒፎርም ማዘጋጀት፣

በ) መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሞተር ተንቀሳቃሽ ከሆነ ሙሉ ነጭ ቀለም ዩኒፎርም ማዘጋጀት፣

3. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ጠብቆ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ የሆነ፣
4. በከተማው ውስጥ ለግል አገልግሎት ለማዋል በኮድ 2 የተመዘገቡ፣ የንግድ ወይም የማህራት፣ የድርጅት፣ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሞተር ሳይክሎች ጂፒኤስ ገጥመው መገኘት፡፡

## 7 የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርም

1. በከተማዋ የዕቃ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል አሽርካሪዎች አንፀባራቂ ያለው አንድ ዓይነት የሆነ የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርም ይለብሳሉ፤
2. የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርሙ በሌላ መደበኛ ልብስ ላይ በመደረብ የሚለበስ ቀላልና ከፊት እና ከኃላው የዳማ ቀለም ወይም የቼዝ መጫወቻ ዓይነት ሲሆን የምሽት አንፀባራቂ በአግድም የተለጠፈበት ነው፤
3. ዩኒፎርሙ ያልተቀደደ፣ ንጹህ፣ ትክክለኛ ይዘቱን የጠበቀ እና ጀርባው ላይ የሚቀመጠው ጹሁፍ ከርቀት የሚለይ መሆን አለበት፡፡

## 8 የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን

1. ዕቃ የሚያመላልሱ ሞተር ብስክሌቶች እና የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል ዕቃውን የሚይዙበት ሳጥን 50 ሳ.ሜ x 46 ሳ.ሜ x 46 ሳ.ሜ ያልበለጠ መጠን እንዲሁም ዝናብ በማያስገባ ሁኔታ በብረት ወይም በፕላስቲክ የተሰራ መሆን አለበት፤
2. የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ተመሳሳይ እይታ እንዲኖረው በሚያስችል ሁኔታ እንደ ሞተር ሳይክሉ እና የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል ቀለም ቢጫና ሰማያዊ ወይም

በተቋሙ ሎጎ ቀለም 6 ሳ.ሜ በ6 ሳ.ሜ ዳማ በሆነ በማይለቅ ቀለም መቀባት አለበት፡፡

9 **የጭንቅላት ደህንነት መከላከያ**

1. ሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል አሽከርካሪ ደህንነቱን ለመጠበቅ የሚረዱ የጭንቅላት እና ሌሎች የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች መጠቀም አለበት፤
2. የጭንቅላት ደህንነት መከላከያ ለሞተር ሳይክል ወይም ለኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል አሽከርካሪ ተብሎ በስታንዳርድ መሰረት የተዘጋጀ ብቻ መሆን አለበት፡፡

10 **የፍጥነት ወሰን**

በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የከተማዋ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ የሞተር ሳይክል የፍጥነት ወሰን 50 ኪሎ ሜትር በሰዓት ነው፡፡

11 **ስለትራንስፖርት ማህበራት**

1. ማንኛውም ነባር የሞተር ብስክሌት አገልግሎት ሰጪ ማህበር በቢሮው ህጋዊ ሆኖ ዕውቅና ሊሰጠው የሚችለው ዝቅተኛው የአባላት ቁጥር 250 (ሁለት መቶ ሃምሳ) አባላት እና ከዚያ በላይ ሲኖረው ነው፤
2. ማንኛውም አዲስ ሞተር ሳይክል ይዞ ለመቅረብ የሚፈልግ ማህበር በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሞተር ሳይክሎች የኤሌክትሪክ ብቻ መሆን አለባቸው፤
3. በልዩ ሁኔታ አገልግሎቱ እንዲፈቀድላቸው የተዘረዘሩት ተቋማት አገልግሎቱ የሚፈቀድላቸው የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ዓይነት ስለመወሰን

12 **የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ዝርዝር መግለጫ**

በሞተር ሳይክል ላይ የሚገጠመው የመቆጣጠሪያ እና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ወይም ጂፒኤስ ዝርዝር መግለጫ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ነጥቦች ማሟላት ይኖርበታል፡-

1. በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ያለበትን ቦታ እና ሁኔታ በግልፅ ሊያሳይ የሚችል፤
2. በባለስልጣኑ እውቅና ከተሰጠው የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅት የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ፤
3. ሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ቢያንስ ሲሄድበት የነበረውን ፍጥነት፣ የተቀንሳቀሰበትን ቀን፣ ሰዓት፣ ዓመተ ምህረት እንዲሁም የተንቀሳቀሰበትን አካባቢ ትክክለኛ መረጃ እንዲሁም የነበረበትን ቦታ ማሳየት የሚችልና መስጠት የሚችል፤
4. ሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል በቀላሉ የሚለይበት የራሱ የሆነ የተለየ የመለያ ቁጥር እና ሌሎች መለያ ኮዶች የያዘ፤
5. ቴክኖሎጂው ቢያንስ በሀገሪቱ ያለውን ዝቅተኛ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ መስፈርት ያሟላ መሆኑን ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የሚያቀርብ፤
6. እያንዳንዱን መረጃ የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ሙሉ እንቅስቃሴ በማያቋርጥ ሁኔታ በግልፅ የሚያሳይ፤
7. በተለያዩ ምክንያቶች የኃይል መቆራረጥ ቢያጋጥም ወይም ጉዳት ቢደርስ ቢያንስ ለ15 (ለአስራ አምስት) ቀናት ያህል ሙሉ እንቅስቃሴ የሚያሳይ እና ማሳወቅ የሚችል፤
8. ከከፍተኛ የፍጥነት ወሰን 50 ኪ/ሜ በሰዓት በላይ ሲያሽከረክር የቀይ መብራት ማሳየት የሚችል ሆኖ የፍጥነት ወሰኑን ሲያልፍ ቢያንስ ከ 5 ሰከንድ ቆይታ በኃላ ያለማቋረጥ ቀይ መብራት ምልክት በጉልህ እንዲያሳይ ሆኖ የተዘጋጀ፤
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የጥፋት አመላካች ቀይ መብራት ከማዕከል በመሆን ቀይ እንዲያበራ ማድረግ የሚችል፤
10. በማንኛውም ሰዓት አሽከርካሪው ከተወሰነው የፍጥነት ገደብ በላይ በመንዳቱ ሞተር ሳይክሉ ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ቀይ በርቶ ሲያገኝ መጀመሪያ ቅጣቱን በመክፈል ለባለስልጣኑ በአካል ቀርቦ እንዲጠፋለት ማድረግ፤

11. ማንኛውም ማህበር ወይም ድርጅት ባለስልጣኑ ውል ከገባባቸው ቴክኖሎጅ አቅራቢ ተቋማት ጋር ብቻ ውል መያዝ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ኃላፊነት

### 13 የቢሮው ኃላፊነት

1. በከተማው የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ባለንብረቶችን አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲደራጅ ያደርጋል፣ የተደራጁ ማህበራት እና የንግድ ፈቃድ ለሚያቀርቡ ድርጅቶች ከመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ማረጋገጫ ሲያቀርቡ የኦፕሬተርነት ፍቃድ ይሰጣል፤
2. በከተማው የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሞተር ሳይክል ማህበራት እና ድርጅቶች በየዓመቱ ከመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ማረጋገጫ ሲያቀርቡ እና በመመዘኛ መስፈርት ወይም ቼክ ሊስት መሰረት የምዘና ሂደቱን ሲያልፍ የኦፕሬተርነት ፍቃድ ያድሳል፤
3. በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በየዓመቱ የምዝገባ ፍቃድ ያላሳደሰ ማህበር ወይም ድርጅት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጥ ይከለክላል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤
4. በሞተር ሳይክል እና በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የአገልግሎት አሰጣጥን በየወቅቱ በመከታተል፣ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አስፈላጊ አቅጣጫዎችን ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
5. በትራንስፖርት አገልግሎት ማህበር የተደራጀ ማንኛዉም አባል ከሌላ ማህበር ጋር ለመደራጅት ቢፈለግ ከዚህ በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ከሚሰጥበት ማህበር ሕጋዊ መሸኛ ደብዳቤ ሲያቀርብ ዝውውሩን ይፈቅዳል፤
6. በሞተር ሳይክል እና በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የአገልግሎት የቅሬታ አፈታት ሥርዓት ይዘረጋል፤
7. በሞተር ሳይክል እና በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያዘጋጃል፣ ያከናውናል፤

8. የቁጥጥር ሠራተኞች በከተማዋ መንገድ ላይ በማሰማራት ወይም በትራፊክ ፖሊስ አማካኝነት የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ትራንስፖርት ሥራ ላይ የቁጥጥር ተግባር ያከናውናል፣ ጥፋት ተፈፅሞ ሲያገኝም ተቆጣጣሪው ወዲያውኑ የክስ ቻርጅ ወረቀት በመሙላት ለተከሳሹ አስፈርሞ ይሰጣል፤
9. በቁጥጥር ወቅት ህጋዊ ማስረጃዎች ያልያዙ እና በህገወጥ መንገድ አገልግሎት ሲሠጥ የተገኘን የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪውን የማሰር እና ስለጥፋቱ በወንጀል እንዲጠየቅ ለሚመለከተው አካል የማቅርብ ኃላፊነት አለበት፡፡

14 የባለስልጣኑ ኃላፊነት

1. በሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ላይ የተገጠሙ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎችና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂዎች በተቀመጠው ዝርዝር መግለጫ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. ተገቢውን ግዴታ እንዲገቡ በማድረግ ፈቃድ እንዲያገኙ ለቢሮው ያስውቃል፤
3. ጂፒኤስ ስለመግጠሙ፣ ቦሎ ስለማድረጉ እና ለማህበር ሞተሮች የማህበር አባልነት የምዝገባ ማረጋገጫ ሲያቀርብ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይሰጣል፤
4. የመከታተያ ሥርዓቱን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ፈቃድ በወሰዱ አካላት ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤
5. የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ለሚያስፈልጋቸው ተጠቃሚዎች የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፤
6. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ ተጠቃሚዎች ቴክኖሎጂውን በሚያሽከረክሩት ሞተር ሳይክልም ሆነ በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ላይ በአግባቡ በመግጠም በከተማው ሰላማዊ በሆነ መልኩ መንቀሳቀሳቸውን እንዲሁም በከተማዋ ለማሽከርከር በተፈቀደው የፍጥነት ወሰን እያሽከረከሩ መሆናቸውን ያረጋጣል፤
7. የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ዕቃዎችን ዓይነት፣ ባለቤት፣ ቦታና የመሳሰሉትን መረጃዎች የያዘ መረጃ እንዲደራጅ ያደርጋል፤
8. በሞተር ሳይክል እና በኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የትራፊክ ህጎችና ሌሎች የህግ መተላለፎች ሲፈፀሙ ቴክኖሎጂውን በመጠቀም መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ በሕጉ መሠረት የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

9. የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ መረጃውን ለቢሮውና ለመሰል ተቋማት ለክትትል ክፍት ያደርጋል፡፡

## 15 የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

ከማህበር ሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ጋር በተያያዘ ለሚሰጥ የስም ዝውውር አገልግሎት አገልግሎት ጠያቂው አባል ከሆኑበት ማህበር ክሊራንስ እንዲያቀርብ በማድረግ የማህበር ንብረት እና ዕዳ የሌለበት ስለመሆኑ እያረጋገጠ አገልግት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

## 16 የአገልግሎት ሰጪ ማህበር ኃላፊነት

1. በሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል በተያያዘ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በቢሮው የተሰጠው ፈቃድ በማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ መያዝ እና በተቆጣጣሪ ሰራተኞች መረጃውን ሲጠየቁ ፈቃዱን የማሳየት፤
2. ማንኛውም የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት ፈቃድ ሳይወስዱ አገልግሎት አለመስጠት፤
3. የኦፕሬተሩ ፍቃድ የሚቀየር ከሆነ ሥራ ከማቆሙ ከ15 ቀን በፊት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ለሰጠው አካላት ማሳወቅ፤
4. የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አዲስም ሆነ ሲጠገን በዚህ መመሪያና በሌላም ሕግ ከተቀመጠው መስፈርት ውጪ ሲሆን አግባብ ላለው አካል ማሳወቅ፤
5. አግባብ ካለው አካል በልዩ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ማኀበር እና ድርጅት ከተፈቀደለት የሞተር ሳይክልም ሆነ የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪዎች ዝርዝርና ብዛት ውጭ አለማሳተፍ፤
6. ደህንነቱ እና ምቾቱ የተጠበቀ የሞተር ሳይክል እናኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ አገልግሎት የማቅረብ፤
7. ለአገልግሎት የሚውሉ የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪዎች የወቅቱን ሙሉ ኢንሹራንስ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤
8. ተገልጋዩ ያለበትን ግዴታና መብቱን የማሳወቅ እና ተፈፃሚነቱን የመከታተልና የመቆጣጠር፤

9. በራሳቸው ወጪ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ መሳሪያና መሳሪያው የሚልከውን መረጃ መከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ ማስገጠም፤
10. በራሳቸው ወጪ ከመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂው በተጨማሪ የሞተረኛውን አግባባዊ የፍጥነት እንቅስቃሴ የሚያሳይ መብራት አብሮ ማስገጠም፤
11. ባለስልጣኑ ካረጋገጠውና ፍቃድ ከሰጣቸው እንዲሁም ከባለስልጣኑ ጋር ግዴታ ከገቡ የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ አልሚዎች ጋር ብቻ ውል በመግባት ቴክኖሎጅ ማስገጠም፤
12. ተጠቃሚው ፈቃድ ሲያገኝ በሰጠው አድራሻ መሠረት ለማንኛውም ጉዳይ በባለስልጣኑም ሆነ በቢሮው ሲፈለግ የመቅረብና የአድራሻ ለውጥም ካደረገ የማሳወቅ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## 17 የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅት ኃላፊነት

1. የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂን የሚያቀርበው ተቋም በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሠረት የተመዘገበና የታደሰ ፈቃድ ያለው እንዲሁም ከባለስልጣኑ ጋር የግዴታ ውል መግባት፤
2. የሀገሪቱን የመረጃ ደህንነት ጠብቆ መስራት፤
3. ለባለስልጣኑ ማንኛውንም የሞተረኛ መረጃ ማቅረብ፤
4. ከተጠቃሚ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ከውሉ ውጭ አለመጠቀም፤
5. ከተጠቃሚ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ቢያንስ ለአንድ ዓመት መያዝ የሚችል የመረጃ ቋት በአገር ውስጥ ሊኖረውና ሙሉውን መረጃ ለባለስልጣኑ በተፈለገው ጊዜ ማቅረብ፤
6. ውል ያስገባውን የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተጠቃሚ በውሉ መሠረት መቆጣጠር ካልቻለ ውል የገቡ ተጠቃሚዎችን ያለ ምንም ተጨማሪ ክፍያ ወደ ሌላ በባለስልጣኑ እውቅና ለተሰጠው አቅራቢ ድርጅት ማዛወር፤
7. ባለስልጣኑ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ ማቅረብ፤
8. በገባው ግዴታ መሠረት ለባለስልጣኑ መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂውን የማየትና መረጃ የማግኘት መብት መስጠት፤

9. የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ የማደስ፤
10. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂን ከመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ጋር ሳይገጥሙ በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ላይ አለመንቀሳቀስ፤
11. በባለስልጣኑ ፍላጎት መሰረት በየትኛውም ጊዜ በመቅረብ ተገቢ መረጃ መስጠት፤
12. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከባለስልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ አለመቀየር፤
13. በማንኛውም ሁኔታ የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ አለማጥፋት ወይም አለማበላሸት፡፡

## 18 የመቆጣጠርያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ ወይም ጂፒኤስ አቅራቢ ድርጅት ኃላፊነት

1. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂው ሁልጊዜ ስራ ላይ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. ከሞተር ሳይክል ተጠቃሚዎች ጋር ውል ሲገባ በዚህ መመሪያ የተፈቀደውን የፍጥነት ወሰን አክብሮ እንዲንቀሳቀስ ግዴታ ይገባል፤ ከፍጥነት ወሰን በላይ ሲያሽከረክርም ምልክት ለባለስልጣኑ እንደሚሰጥ በማድረግ ሊያሳውቀው ይገባል፤
3. የተገጠመው የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅ ላይ ብልሽት ሲጋጥም ብልሽቱን በፍጥነት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
4. በማንኛውም ሁኔታ የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ አለማጥፋት ወይም አለማበላሸት፤
5. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከባለስልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ አለመቀየር፤
6. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ አለማጥፋት ወይም አለመቀየር፤
7. እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር ከሚያስችለው ሥርዓት ጋር የሚናበብ እና ስርዓቱ ተቀባይነት ያለው የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂን ብቻ መጠቀም፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለተከለከሉ ተግባራትና ቅጣት

**19 የተከለከሉ ተግባራት፡-**

የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1. ማንኛውም የሞተር ሳይክል ወይም የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ መንገደኞችን በክፍያ ከቦታ ቦታ የማመላለስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም የሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚሳተፍ ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው አገልግሎት መስጠት፤
3. የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ በመመሪያው መሰረት የተዘጋጀ የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርም በአግባቡ አለመልበሰ፤
4. የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ የቆሸሸ፣ የተቀደደ፣ ይዘቱን ያልጠበቀ እና ጀርባው ላይ የሚቀመጠው ጽሁፍ ከርቀት የማይለይ የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርም ለብሶ ማሽከርከር፤
5. በሚመለከተው አካል ከተቀመጠው የድምጽ ስታንዳርድ በላይ ሙዚቃ ከፍቶ ማሽከርከር፤
6. በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው የዕቃ መጫኛ ውጭ ዕቃ መጫን፤
7. ለሞተር ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ ተብሎ በስታንዳርዱ መሰረት የተዘጋጀ የጭንቅላት ደህንነት መጠበቂያ ሳያደርግ ወይም አድርጎ ሳያስር ወይም የጫነው ሰው ማድረጉንና ማሰሩን ሳያረጋግጥ ማሽከርከር፤
8. ህጋዊ የሆነ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ኖሮት ሳይዝ ማሽከርከር ወይም በወቅቱ አለማሳደስ፤
9. ለሌላ ተሽከርካሪ የተሰጠ ፈቃድን እንደራስ አስመስሎ መጠቀም፤
10. የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፤

11. የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም ጊዜው ያለፈበት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ መንቀሳቀስ፤
12. ህጋዊ ያልሆነ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ መገኘት እና መጠቀም፤
13. ፈቃዱን አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፤
14. ማንኛውም ኦፕሬተር ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል ያሳያቸው መመዘኛዎች በክትትል እና ቁጥጥር ወቅት ተሟልተው አለመገኘት፤
15. አግባብነት ካለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዓይነት ውጭ እንዲሠማራ በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎት አሠጣጥ ላይ መገኘት እና አፈፃፀሙን ማዛባት፤
16. በዚህ መመሪያ የወጣውን መመዘኛ ያላሟሉ በተለያዩ የዲሲፒሊን ጉድለት ምክንያት የተቀጡ እና የታገዱ የሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎችን መቅጠር፤
17. በሥራ ላይ እያለ አግባብ ባላቸው የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፤
18. በትራንስፖርት ተቆጣጣሪ እንዲቆም ሲጠየቅ ለመቆም ፈቃደኛ አለመሆን፤
19. የእንቅስቃሴ ክልከላ ወይም ገደብ በተጣለበት ወቅት ሲንቀሳቀስ መገኘት፤
20. የመቆጣጠሪያ መሳሪያ ወይም ጂፒኤስ መንቀል ወይም ከአገልግሎት ውጪ ማድረግ፤
21. የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ አለማደስ፤
22. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ከመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ ጋር ሳይገጥም መንቀሳቀስ፤
23. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ ማጥፋት ወይም መቀየር፤
24. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጂ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከባለስልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ መቀየር፡፡

## 20 ስለ አስተዳደራዊ ቅጣት

1. በሌላ ሕግ የተጣሉ ጥፋቶችና ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 20 የተከለከሉ ተግባራትን የፈፀመ የሞተር ሳይክል እና የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ አሽከርከሪ በጥፋቱ አይነት ቅጣት ይጣልበታል፤
2. የጥፋት ዓይነትና በደረጃ እና እንደጥፋቱ ክብደት የሚጣሉ ቅጣቶች በግልፅ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 21 ደረጃ አንድ የጥፋት ዓይነት

ማንኛውም፡-

1. የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ በመመሪያው መሰረት የተዘጋጀ የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርም በአግባቡ ያልለበሰ፤
2. በመመሪያው መሰረት ህጋዊ የሆነ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ኖሮት ሳይዝ ያሽከረከረ ወይም በወቅቱ ያላደሰ፤
3. የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ የቆሸሸ፣ የተቀደደ፣ ይዘቱን ያልጠበቀ እና ጀርባው ላይ የሚቀመጠው ጹሁፍ ከርቀት የማይለይ የሥራ ልብስ ወይም ዩኒፎርም ለብሶ ያሽከረከረ፤
4. በሚመለከተው አካል ከተቀመጠው የድምጽ ስታንዳርድ በላይ ሙዚቃ ከፍቶ ያሽከረከረ፤
5. በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው የዕቃ መጫኛ ውጭ ዕቃ የጫነ፤
6. ለሞተር ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ ተብሎ በስታንዳርዱ መሰረት የተዘጋጀ የጭንቅላት ደህንነት መጠበቂያ ሳያደርግ ወይም አድርጎ ሳያስር ወይም የጫነው ሰው ማድረጉንና ማሰሩን ሳያረጋግጥ ያሽከረከረ፤ እንደሆነ የ500.00 ብር (አምስት መቶ ብር ብቻ) ቅጣት ይጣልበታል፡፡

22 ደረጃ ሁለት የጥፋት ዓይነት

ማንኛውም፡-

የሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ትራንስፖርት አሰጣጥ ላይ የሚውሉ ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው አገልግሎት የሰጠ፤

1. የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም ጊዜው ያለፈበት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ የተንቀሳቀሰ፤
2. የሞተር ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አገልግሎት ሰጪ ማህበር፣ ድርጅት ፈቃዱን አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ፣
3. በትራንስፖርት ተቆጣጣሪ እንዲቆም ሲጠየቅ ለመቆም ፈቃደኛ ባለመሆን አምልጦ የሄደ፤
4. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከባለስልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ የቀየረ፤እንደሆነ የ1,000.00 ብር (አንድ ሺህ ብር ብቻ) ቅጣት ይጣልበታል፡፡

23 ደረጃ ሦስት የጥፋት ዓይነት

1. በሥራ ላይ እያለ አግባብ ባላቸው የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ፤
2. አግባብ ካለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር የሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዓይነት ውጭ እንዲሠማራ በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎት አሠጣጥ ላይ መገኘት እና አፈፃፀሙን ያዛባ፤ እንደሆነ የ1,500.00 ብር (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ብቻ) ቅጣት ይጣልበታል፡፡

24 ደረጃ አራት የጥፋት ዓይነት

ማንኛውም፡-

1. በዚህ መመሪያ የወጣውን መመዘኛ ያላሟሉ በተለያዩ የዲሲፒሊን ጉድለት ምክንያት የተቀጡ እና የታገዱ የሞተር ሳይክል ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎችን የቀጠረ፤

2. የሞተር ወይም ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አገልግሎት ሰጪ ማህበር፣ ድርጅት ፈቃዱን አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ፤
3. የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ ያላደሰ፤
4. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ከመከታተያ ሥርዓት ቴክኖሎጅ ጋር ሳይገጥም በከተማ የተለያዩ ቦታዎች ላይ የተንቀሳሰቀ፤ እንደሆነ የ2,000.00 ብር (ሁለት ሺህ ብር ብቻ) ቅጣት ይጣልበታል፡፡

## 25 ደረጃ አምስት የጥፋት ዓይነት

ማንኛውም የሞተር ወይም የኤልክትሪክ ሳይክል አሽከርካሪ፡-

1. ህጋዊ ያልሆነ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ የተገኘ እና የተጠቀመ፤
2. የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ፤
3. የመቆጣጠሪያ መሳሪያ ወይም ጂፒኤስ የነቀለ ወይም ከአገልግሎት ውጪ ያደረገ፤
4. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ ያጠፋ ወይም የቀየረ፤ እንደሆነ የ4,000.00 ብር (አራት ሺህ ብር ብቻ) ቅጣት ይጣልበታል፡፡

## 26 ደረጃ ስድስት የጥፋት አይነት

ማንኛውም የሞተር ወይም የኤልክትሪክ ሳይክል አሽከርካሪ፡-

1. የእንቅስቃሴ ክልከላ ወይም ገደብ በተጣለበት ወቅት ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፣
2. ለሌላ ተሽከርካሪ የተሰጠ ፈቃድን እንደራስ አስመስሎ ከተጠቀመ እና
3. ማንኛውም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው አካል ላይ ቀላል ጉዳት ያስከተለ፣ የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ለ 3 ወራት የጊዜ ገደብ ይታገዳል፡፡

## 27 መረጃ አያያዝ

በዚህ በአንቀጽ 20(2) መሠረት የሚዘጋጀው የጥፋተኝነት ክስ ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

1. የአሽከርካሪው ስም፤
2. የመንጃ ፈቃድ ቁጥር፤
3. የሞተር ሠሌዳ ቁጥር፤
4. ደንብ የተጣሰበትን ሰዓት፣ ቦታና ቀን፤
5. የተፈፀመውን የጥፋት ዓይነት እና እርከን፤
6. የትራፊክ ፖሊሱ ወይም የተቆጣጣሪው ሙሉ ስምና ፊርማ፤

7. ደንብ ተላላፊው በቅፁ ቀሪ ገጽ ላይ እንዲፈርም በማድረግና የመንጃ ፈቃዱን በማስረጃነት በመያዝ አንድ ኮፒ የጥፋተኝነት ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

28 **ፈቃድ የሚያሰርዝ የጥፋት አይነት**

ማንኛውም የሞተር ወይም የኤልክትሪክ ሳይክል አሽከርካሪ፡-

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ታግዶበት እያለ ሲያሽከረክር የተገኘ
2. ማንኛውም አይነት ጥፋት በመፈፀም በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ያስከተለ፣
3. ማንኛውም አይነት ጥፋት በመፈፀም የሰው ህይወት እንዲያልፍ ያደረገ፣

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29 **አቤቱታ ስለማቅረብ**

በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰደው እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፡-

1. እርምጃው በተወሰደ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለሚመለከተው አስፈፃሚ አካል የትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ ለቅርንጫፍ የትራፊክ ማኔጅመንት ጽ/ቤት፣ ለአሽከርሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፤
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሱት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የበላይ ኃላፊ አቤቱታው በቀረበለት በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ውሳኔውንም በጽሁፍ አድርጎ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤
3. አቤቱታ አቅራቢው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው ወይም በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሱት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠሪ ቢሮዎች ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
4. አቤቱታ አቅራቢው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው ወይም በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ፍርድ ቤት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

30 **ስላልተመዘገቡና ሰሌዳ ሰለሌላቸው የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክሎች**

1.በከተማው የሚንቀሳቀሱ በአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ሳይመዘገቡ እና ሰሌዳ ሳይኖራቸው አገልግሎት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ

የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክሎች በአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የተቀመጠውን መመዘኛ መስፈርት ሲያሟሉ የሰሌዳ አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ ተመዝግቦ አገልግሎት ለመስጠት አዲስ የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ለኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል አገልግሎት ብቻ ነው፡፡ ይህ መመሪያ ከወጣ በኋላ ለሞተር ሳይክል አገልግሎት ፈቃድ አይሰጥም፡፡

## 31 የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ማህበራትና ግለሰቦች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 32 ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

1. የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈፀሚያ መመርያ ቁጥር 04/2011 በዚህ መመርያ ተሽሯል፤
2. ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም በቢሮው የወጣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 33 መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል በማንኛውም ጊዜ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 34 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የአፈፃፀም መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ 2016 ዓ/ም**

**ምትኩ አስማረ ሰጠኝ**

**የአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ**